# የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ጉዞ ከየት ወዴት እና የፖሊሲ ትግበራ ችግሮች

ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

# ይዘት

- መግቢያ
- የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ጉዞ ከየት ወዴት እና የፖሊሲ ትግበራ ችግሮች
- እስካሁን ያሳካናቸው የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች
- የትምህርትና ሥልጠና ችግሮችና ተግዳሮቶች
  – አጠቃላይ ትምህርት
  – ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
  – ከፍተኛ ትምህርት
- ማጠቃለያ

# መግቢያ

- አንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል እምቅ አቅም ነው፡፡
- ዛሬ በሣይንስና ቴክኖሎጂ በልጽገው በአገራቸው ልማትን በማምጣት የሕዝባቸውን ተጠቃሚነት ያጐለበቱ አገሮች ልምድ የሚያሳየን ይህን ሐቅ ነው፡፡
- በተለይ በቅርብ አመታት ከነበሩበት የድህነት አረንቋ ወጥተው ከፍተኛ የሣይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ላይ የደረሱ የደቡብ ኮሪያ፣ የቻይና፣ የሲንጋፖር፣ የቬትናም፣ የማሌዢያ፣ ወዘተ. አገሮች ተሞክሮ እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

## የቀጠለ…

- በአገራችንም መንግሥት በ1986 ዓ.ም. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊስ በመቅረጽ ሰብአዊ ሀብትን በማልማት ሀገራችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው፤ ሩቅ ባልሆነ ጊዜም ከበለፀጉት አገሮች ተርታ ለማሳለፍ መሠረታዊ መሆኑን በመረዳት ለትምህርትና ሥልጠና ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡
- በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው የተቀመጠውን አላማና ግብ ለማሳካት ባለፉት 24 አመታት የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነትና ጥራት ለማጐልበት ሰፊ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡
- ፖሊሰውን መሠረት ያደረጉ፤
  - የትምህርት ስታንደርዶች፣
  - ስትራቴጂዎች፣ የትምህርት ልማት መርሃ ግብሮች (ESDP I-V)፣

  ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫዎች ጋር በማስተሳሰርና በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

## የቀጠለ...

- በሁሉም ዘርፎች የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በማስፋፋት የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነትን በማጐልበት በኲል በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

- በተለያዩ ዘርፎች ባለሙያዎችን በማፍራት አገራችን አሁን ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ የበኲላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

- ምንም እንኳን ባለፉት ሃያ አራት አመታት የትምህርትና ሥልጠና ውጤቶችን ያስመዘገብን ቢሆንም፤
  - በፖሊሲው መሠረት ባለመፈፀም፣
  - በየደረጃው በፖሊሲው ላይ ግልጽነት ባለመፍጠራችንና በአግባቡ መተግበር ባለመቻላችን
  - እስካሁን ያልፈታናቸው
    - የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና አግባብነት ችግሮችና ተግዳሮቶች አሉ፡፡

የቀጠለ...

- እነዚህ ችግሮች አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛል፡፡
- በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በመፍታት የትምህርትና ሥልጠና ጥራት እንዲሻሻልና ተገቢነቱ እንዲረጋገጥ የተቀናጁ ጥረቶች ሊደረጉ ይገባል፡፡
- ችግሮቹ አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡
- በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ይቻል ዘንድ የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ–ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እየተሠራ ይገኛል፡፡
- ለፍኖተ–ካርታው ግብአት የሚሆን ጥናት እንዲጠና ተደርጓል፡፡

# 1. የዘመናዊ ትምህርት አጀማመርና ዕድገት በኢትዮጵያ (አጭር ቅኝት)

## 1.1 የትምህርት አጀማመር

- በሀገራችን ልዩ ልዩ የሃይማኖት ተቋማት እምነታቸውን ለማስፋፋት ከረዥም ዓመታት በፊት ጀምሮ ባሕላዊ የሃይማኖት ትምህርት ይሰጡ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

- በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን **የጀስዊትስ ሚሲዮናውያን** ዘመናዊ ትምህርትን ለማስጀመር ያደረጉት ጥረት **የንጉስ ሱስንዮስን** ከሥልጣን መውረድ ተከትሎ ሚስዮናውያኑ ከሀገር እንዲወጡ ሲደረግ ተቋርጧል ፡፡

- በ1812 ዓ.ም አካባቢ በሚሲዮናውያንን አማካይነት እንደገና ከእምነት ጋር የተሳሰረ ዘመናዊ ትምህርት ለማስጀመር የተሞከረ ቢሆንም በወቅቱ በተለይ የክርስትና እምነት መሪዎች “ ሀገሪቱን ወደ ካቶሊክነት የሚቀይር ነው” በሚል ስጋት ባስነሱት ተቃውሞ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡

የቀጠለ…

- እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ትምህርት ለሃይማኖት ተቋማት የተተወ ስለነበር መንግሥት አቅርቦትን ለማስፋፋትም ሆነ በእነዚህ ተቋማት የሚሰጠው ትምህርት የሀገርን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት የሚያሟላና ተገቢነት ያለው እንዲሆን ያደረገው ጥረት አልነበረም፡፡
- በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተከሰቱ ሁኔታዎች የዘመናዊ ትምህርትን አስፈላጊነት ይበልጥ አጉልተው በማሳየታቸው ቀድሞ የነበረው አመለካከት መቀየር ጀመረ፡፡
- ሀገራችን በ1888 የጣሊያን ወራሪ ሠራዊትን **አድዋ** ላይ ድል በማድረጓ የአውሮፖ ሀገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለመፍጠርና ልዩ ልዩ የትብብር ስምምነቶችን ለመፈራረም ፍላጎት አሳይተዋል፡፡
- ይህም ሁኔታ የተዛባውን አመለካከት በመቀየር ለትምህርት ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያደረጉ አጋጣሚዎችን ፈጥሯል፡፡
- **ኢትዮጵያ ነፃነቷን በአስተማማኝ ደረጃ ማስከበር እንድትችል፣ የቤተክህነት ትምህርት በቂ እንዳልሆነ፣ ሀገሪቱን ለመገንባትና በአውሮፖውያን ዐይን ጠንካራ መንግሥት ሆና እንድትቆይ ዘመናዊ ትምህርት እንደሚያስፈልግ ተረዱ፡፡**

የቀጠለ…

- በአጠቃላይ በወቅቱ የመንግሥት ቢሮክራሲ እየሰፋ በመሄዱና ዘመናዊ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት / የስልክ ፣ የትራንስፖርት ፣ የምድር ባቡር ፣ ወዘተ./ በመደራጀታቸው በነዚህ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ለማፍራት የዘመናዊ ትምህርት አስፈላጊነት ከቀድሞው ይበልጥ እየጨመረ መጥቷል፡፡
- አፄ ምኒልክ የመጀመሪያውን የትምህርት አዋጅ በ1898 ዓ.ም አውጥተው በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ታሪክ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ከሁለት ዓመት በኃላ በ1900 ዓ.ም ተከፍቶ ዘመናዊ ትምህርት አሀዱ ተብሎ ተጀመረ፡፡

- በወቅቱ በሃይማኖት ተቋማት በኩል ለዘመናዊ ትምህርት በነበረው አሉታዊ አመለካከት የተነሳ በሕዝቡ ዘንድ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት የመላክም ሆነ የመማር ፍላጎት አልነበረም፡፡

የቀጠለ...

- የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ሲከፈት 100 ያህል ተማሪዎች እነሱም የመሳፍንትና የመኳንንት ልጆች ብቻ ነበሩ፡፡
- በ1912 ዓ.ም Ernest Work የተባሉ ጥቁር አሜሪካዊ ፕሮፌሰር በሀገሪቱ ይሰጥ የነበረውን የትምህርት ሁኔታ ከገመገሙ በኃላ የትምህርት ሥርዓቱ እንዲቀየር የበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡
- **ምሁሩ በአስተያየታቸው ትምህርቱ የሚሰጠው፡-**
  - በውጭ ሀገር መምህራን በውጭ ቋንቋ መሆኑን፣
  - ይዘቱም አውሮፓዊ ቋንቋን በማስተማር፣ በአውሮፖ ታሪክና ባሕል ላይ ያተኮረ፣
  - ስለሀገር ውስጥ ሁኔታና ፍላጎት እንዲሁም ለሙያ ሥልጠና ግምት ያልሰጠ መሆኑን በመተቸት እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት ለሀገር እድገት ፋይዳ እንደማይኖረው ገልጸዋል፡፡

የቀጠለ...

- ከአፄ ምኒልክ ሞት በኋላ ንግስት ዘውዲቱ በ1921ዓ.ም ከቤተክርስቲያን ትምህርት ጋር የሚጣጣም ትምህርት እንዲሰጥና ልጅ ያለው ሁሉ ልጁን እንዲያስተምር የሚያስገድድ አዋጅ አውጥተው ነበር፡፡

- አፄ ኃይለሥላሴ ንጉሡ ነገስት ከሆኑ በኋላ ከ1923-1928 ዓ.ም ድረስ አምስት ዓመታት ተጨማሪ 20 ትምህርት ቤቶች (የእቴጌ መነን ት/ቤት ጨምሮ) በአዲስ አበባና በጠቅላይ ግዛቶች ተከፍተው ነበር፡፡

- ይሁን እንጂ የፐሮፌሰር Work አስተያዬት ተግባራዊ ሳይደረግ በፋሺስት ጣሊያን ወረራ ምክንያት ዘመናዊ ትምህርት በእንጭጩ ተስተጓጐለ፡፡

## 1.2. ትምህርት ከ1933 ዓ.ም - 1966 ዓ.ም

- የጣሊያን ወረራ በሀገሪቱ ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት ሙሉ በሙሉ አዳፍኖት ነበር፡፡
- በጣሊያን ወረራ ወቅት
  - ትምህርት ቤቶችና የትምህርት መሣሪያዎች በመውደማቸው፣
  - በጊዜው የነበሩ ጥቂት መምህራን በጦርነቱ ምክንያት በመሰደዳቸውና በመሞታቸው
  - 4,200 ያህል ተማሪዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲበተኑ በመደረጉ በጥቂቱም ቢሆን
  - የነበረው የዘመናዊ ትምህርት ጭላንጭል ሙሉ በሙሉ በመጨለሙ ከድል በኋላ ከባዶ መጀመር ግድ ሆኖ ነበር፡፡
- በተለይ በአዲስ በተቋቋሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተለያዩ ደረጃ ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩትን የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያውያን መተካት ዋነኛ ግቡ ነበር፡፡

የቀጠለ...

- በ1934 ትምህርት ሚኒስቴር እንደገና ተቋቁሞ ከታላቋ ብሪታኒያና በወቅቱ የብሪታኒያ ቅኝ ግዛት ከነበሩት ሀገሮች በመጡ የትምህርት ባለሙያዎች የሚመራ ትምህርት በብሪታንያ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት መሰጠት ተጀምሮ ነበር፡፡
- በ1943ዓ.ም የመጀመሪያው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡
- በ1943 ዓ.ም ነሐሴ 8 ቀን በኢትዮጽያና በአሜሪካ መንግስት መካከል የተፈረመው "Point Four Programme" በመባል የሚታወቀው የትብብር ስምምነት የሀገሪቱን የትምህርት አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ቀየረው፡፡
- በ1945 ዓ.ም ተግባራዊ መሆን ሲጀምር ቀድሞ በብሪታኒያ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ይመራ የነበረው የትምህርት አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ወደ አሜሪካ የትምህርት ሥርዓት ተቀየረ፡፡ በአሜሪካኖች አማካሪነት በተነደፈው የአምስት ዓመት የትምህርት ዘርፍ ዕቅድ የትምህርቱ ሥራ በተገደበ የማስፋፊያ አቅጣጫ ስልት ("Controlled Expansion") መመራት ጀመረ፡፡
- በ1953 ዓ.ም ዩኔስኮ በአዲስ አበባ ባደረገው ስብሰባ ሂደቱን ገምግሞ ዕቅዱን **በከፍተኛ ሁኔታ ተቃውሞት** ነበር፡፡

የቀጠለ...

## በ1965 የትምህርት ዘርፍ ጥናት (Educatiion Sector Review)

- በዓለም ባንክ ድጋፍ በልዩ ሁኔታ የ31 ዓመት የትምህርት ጉዞ ዳሰሳ ጥናት ተጠና፡፡

- አጥኚዎች፡- የሴክተር ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፣ የኮሚሽኖች፣ የቤተክህነት፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ተወካዮች ሲሆኑ 70% ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡

- የፖሊሲ ዋና ጉዳዮች ፡- የትምህርት እድል ቅድሚያ፣ የትምህርት ዓይነት፣ የተባበረ የስራና የልማት ፕሮግራም፣ የት/ት ዘመን፣ የት/ት ስርጭት፣ የት/ት በጀት፣ የገንዘብ መዋጮና ክፍያ፣ የምምህራን፣ የፈተናና የትምህርት አስተዳደር የሚሉ ነበሩ፡፡
- አፈጻጸም፡- የአጭርና የረዥም ጊዜ የማስፈጸሚያ እቅድ ወጥቶለት ነበር፡፡

- **በ1941 የመምህራን ማህበር ሕብረት** በሚል የተቋቋመው ህብረት በ1965 በህጋዊ አካልነት የኢትዮፕያ መምህራን ማህበር ሆነ፡፡
- **በ1965 የእርባ ምንጬ ጉባዔ** ውሳኔ አስተላልፎ በየካቲት 11 ቀን 1966 ሀገር አቀፍ የስራ ማቆም አድማ በማድረግ አብዮቱን አቀጣጠለ፡፡

# 1.3. ትምህርት በዘመነ ደርግ (1967 - 1983 ዓ.ም)

- በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶሻሊስት ፍልስፍና በማስተማር ተማሪው የኮሚኒዝም ርዕዮተ አለምን በግድ እንዲቀበል የሚያደርግ ትምህርት በቀጥታ ከሶሻሊስት ሀገሮች ተቀድቶ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

- በግል ድርጅቶች፣ በሃይማኖትና በሚሲዮናውያን ተቋማት ይሰጥ የነበረው ትምህርትና ሥልጠና እንዲቋረጥ በማድረግም የትምህርቱን ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲቆጣጠረው ተደርጓል፡፡

- የእድገት በህብረት ዘመቻ መምጣትና 11ኛና 12 ክፍል መቋረጡ፣
- በ1969 የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን በአዋጅ መቋቋሙ እና እስከ 1972 በነባሩ ስርዓተ ትምህርት የሽግግር ስርዓተ ትምህርት ሆኖ መቀጠሉ፣

- 1969- 1972 ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ያጋጠመና ቀጥታ ቅጥር ያለስልጠና የተጀመረበት ፣
- በ 1971 መጠነ ሰፊ የመሰረተ ትምህርት ዘመቻ - በ8 ዓመት ማይምነትን ከኢትዮጵያ ማጥፋት፣
- በ1972 የኢሰፓአኮ 2ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ አቅጣጫ አስቀመጠ፣

የቀጠለ...

- የፖሊቴክኒክ ትምህርት (8-2-2) ፕሮግራም መቀረጽና መጀመር፣
  - የመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ ፖሊቴክኒክ ትምህርት ከ 7 እስከ 14 ዓመት
  - የሁለተኛ ደረጃ አጠቃላይ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ከ15 – 16 ዓመት
  - የተከታይ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ከ17 – 18 ዓመት
  - የተከታታይ ቴክኒክና ሙያ ተምህርት ከ18 ዓመት በላይ

- የፖሊቴክኒክ ስርዓተ ትምህርት፡-
  - በ1973 በአዲስ አበባ በ25 ት/ቤቶች በ1974 በሌሎች 45 ት/ቤቶች፣
  - በድምሩ በ70 ት/ቤቶች በ39 ሺህ ተማሪዎችና በ800 መምህራን ተሞከረ፡

- በ1978 የኢትዮጵያ ትምህርት ጥናታዊ ግምገማ በልዩ ልዩ የትምህርት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ጥናት ተጠንቶ ነበር፡፡

**በደርግ ዘመነ መንግስት የነበሩ የትምህርትና ስልጠና ተግዳሮቶች**

- **የአቅርቦት ውስን መሆን**
- **ኢ-ፍትሐዊ ሥርጭት**
- **የብቃት ችግር**
- **የትምህርት ተገቢነት የማምጣትና የጥራት ችግር**

1.4. የትምህርትና ስልጠና 1984 ዓ.ም

## ከብዙ ጥናትና ውይይት በኋላ በ1986 ዓ.ም የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ወጣ ፡፡

**የፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱን ማን መራው?**

•በሚኒስትሮች ም/ቤት ባለቤትነት የአጠቃላይ ትምህርት ስልጠና ፖሊሲ አጥኚ ግብረ ሀይል፤

**አባላት እነማን ነበሩ?**

•በሚኒስትሮች ም/ቤት ሰብሳቢነት ከት/ሚ/ር(5)፣ ከሚኒስትሮች ም/ቤት(2), አ/አ/ዩ(3)፣ ከፍ/ት/ዋ/መ (1)፣ከግብርና ሚ/ር(1)፣ ከፕ/ኢ/ሚ/ር(1) የተውጣጡ 14 አባላት ነበሩት፡፡

**የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት**

•በት/ት ሚ/ር ሰብሳቢነት ከተለያዩ መ/ቤቶች የተውጣጡ 9 አባላት ያሉበት፡፡

**ፖሊሲው ዝግጅት የተካፈሉ መ/ቤቶች**

•የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ 12 የሴክተር ሚኒስቴር መ/ቤቶች፤ 4 የኮሚሽን መ/ቤቶች፣ 2 የባለስልጣን መ/ቤቶች፣ 2 የምርምር ኢንስቲትዩቶችና የኢትዮጵያመምህራን ማህበር ናቸው፡፡

# ንዑሣን ግብረ ሀይሎች (6)

1. የአጠቃላይ ት/ትና ስልጠና ፖሊሲ ጥናት ፣ የሥርዓተ ትምህርትና የመምህራን ትምህርት ፖሊሲ (8)
2. የትምህርት ምዘና ፖሊሲ (5)
3. የትምህርት እና ቋንቋ ፖሊሲ (4)
4. የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የምርምርና ልማት መስተጋብር ፖሊሲ ጥናት (10)
5. የትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች ፖሊሲ (6)
6. የትምህርት አደረጃጀትና ፋይናንስ ፖሊሲ (9)

# የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ

**5 አላማዎች፣ 15 ዝርዝር ዓለማዎች፣ 9 ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች እና** የአጠቃላይ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም የማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች ነበሩት

1. ሥርዓተ ትምህርት፣
2. ትምህርት ዕርከን፣
3. የትምህርት ምዘና፣
4. የመምህርን ጉዳይ፣
5. ቋንቋና ትምህርት፣
6. የትምህርት ድጋፍ
7. የትምህርት፡ የሥልጠና ፡ የምርምርና ልማት ተስተጋብሮት፣
8. የትምህርት አደረጃጀትና አመራር
9. የትምህርት ፋይናንስ፣

# እስካሁን ያሳካናቸው የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች

- ምንም እንኳን ባለፉት ሃያ አራት አመታት የትምህርትና ሥልጠና ውጤቶችን ያስመዘገብን ቢሆንም፤
  - በፖሊሲው መሠረት ባለመፈፀም፣
  - በየደረጃው በፖሊሲው ላይ ግልጽነት ባለመፍጠራችንና በአግባቡ መተግበር ባለመቻላችን
  - እስካሁን ያልፈታናቸው
- የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና አግባብነት ችግሮቹ አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡
- በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ይቻል ዘንድ የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እየተሠራ ይገኛል፡፡
- ለፍኖተ-ካርታው ግብአት የሚሆን ጥናት እንዲጠና ተደርጓል፡፡
  - ችግሮችና ተግዳሮቶች አሉ፡፡

# የትምህርትና ሥልጠና

## ችግሮችና ተግዳሮቶች

# አጠቃላይ ትምህርት

## ቅድመ መደበኛ








## ትኩረት የተነፈገውና በአግባቡም ያልተተገበረ የቅድመ መደበኛ ትምህርት

- የቅድመ መደበኛ ኘሮግራም አፈጻጸም እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በክልሎች መካከል ያለው የአፈጻጸም ልዩነት እጅግ የከፋና ፍትሐዊነቱ በጣም የሰፋ መሆኑ፣
- ደረጃውን በጠበቀ ሥርዓተ-ትምህርት፣ መምህራንና ተቋማት ያልተመራ መሆኑ፣
- ከአለም አቀፍ (ዩኒስኮ ስታንዳርድ) እና ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በየደረጃው ያለው አመራርም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በእውቀትና በቅንጅት መምራት አለመቻሉ፣

# ትኩረት የተነፈገውና በአግባቡም ያልተተገበረ የቅድመ መደበኛ ትምህርት፡


ከ2005-2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%



| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 25.5 | 33 | 38 | 43.1 | 44.5 |
| ወንድ | 26.6 | 34.9 | 40 | 45.8 | 47.1 |
| ድምር | 26.1 | 34 | 39 | 44.4 | 45.9 |

ሴት ወንድ ድምር


ከ2006-2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ትምህርት የጥቅል ተሳትፎ እድገት ጭማሬ በ%



## እጅግ የከፋና ፍትሐዊነቱ በጣም የሰፋ በክልሎች መካከል የአፈጻጸም ልዩነት፡


### የ2009 ዓ.ም የክልሎች የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%




| | ትግራይ | አፋር | አማራ | አሮሚያ | ኢትዮ-ሶማሌ | ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | ደቡብ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬዳዋ | አገር አቀፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድምር | 93.2 | 11.7 | 45.1 | 31.9 | 7.4 | 40.1 | 72.2 | 25.9 | 90.2 | 92.4 | 53.8 | 45.9 |
| ሴት | 92.9 | 11.7 | 44.6 | 30.5 | 7 | 37.8 | 69.6 | 25 | 88.4 | 91.4 | 53.2 | 44.5 |
| ወንድ | 93.5 | 11.8 | 45.6 | 33.3 | 7.8 | 42.4 | 74.9 | 26.8 | 91.9 | 93.4 | 54.5 | 47.1 |

# ከአለም አቀፍ (ዩኒስኮ ስታንዳርድ) እና ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች በጣም ዝቅተኛ የቅድመ መደበኛ ኘሮግራም አፈጻጸም፤



# የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት






# የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ፕሮግራም

- ፍትሐዊነትን ሙሉ በሙሉ ያላረጋገጠ ኘሮግራም መሆኑ፣
- አሁንም ቢሆን ከትምህርት ገበታ ውጪ ያሉ ሕጻናት መኖር፣
- በአንዳንድ ክልሎች የተሣትፎው ሁኔታ ወደ ኋላ የመመለስ አደጋ መኖር፣
- ከፍትሐዊነት አኳያ አሁንም ክፍቱ፣
  - በአካባቢ /በአርብቶ አደር፣ ነባር ብሔረሰቦች/
  - በጾታ መካከል፣
  - እጅግ በጣም ዝቅተኛ ተሣትፎና ተገቢውን ምላሽ ያልተሰጠው ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕጻናት፣
- ከብቃት አኳያ መጠነ ማቋረጡ እጅግ ከፍተኛና አደጋ መሆኑ፣

## ፍትሐዊነትን ሙሉ በሙሉ ያላረጋገጠ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፡


### የተሣትፎ መጠኑ ከአመት አመት መዋዥቅ የሚታይበት ነው፡፡

ከ2006-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ-8ኛ ክፍል) የተሳትፎ እድገት ጭማሬ በ%



# ከብቃት አኳያ መጠነ ማቋረጡ እጅግ ከፍተኛና አደጋ መሆኑ፣

ከ2005-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሣይክል (5ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 62.2 | 63.4 | 64.8 | 68.9 | 71.4 |
| ወንድ | 63.4 | 64.7 | 67.8 | 73.3 | 77.3 |
| ድምር | 62.8 | 64.1 | 66.3 | 71.1 | 74.4 |

# አሁንም ገና ወደ ት/ቤት ያልመጡ ሕጻናት አሉ

- በዩኒስኮ ሪፖርት መሠረት እ.ኤ.አ በ2015 በአለም ላይ ወደ 264 ሚሊዮን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘት የሚገባቸው ሕጻናትና ወጣቶች ከትምህርት ቤት ውጪ ነበሩ፡፡
  - በ2015 በአለም ላይ እድሜያቸው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ደርሶ ወደ ትምህርት ቤት በመምጣት መማር ሲገባቸው ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ ሕጻናት፤ አንድ ሶስተኛውን ቁጥር የያዙት፤ ናይጄሪያ፣ ፓኪስታን፣ ሕንድ፣ ሱዳን፣ ኢንዶነዢያና ኢትዮጵያ ናቸው፡፡
  - በተለይ ልዩ ፍላጎት ያላቸው፣ የነባር ብሔረሰቦች፣ በገጠር የሚገኙና የሴት ሕጻናት ወደ ትምህርት ቤት አለመምጣት ችግር የከፋ ነው፡፡

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት






# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን


## በጣም አዝጋሚ እድገት እያሳየ ያለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት /9ኛ ክፍል - 10ኛ ክፍል/ ፕሮግራም

ከ2005-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (፱ኛ-፲ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%

ግራፍ 8፣ ከ2005-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%





ግራፍ 9፣ ከ2006-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ እድገት ጭማሬ በ%




| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | | 1.1 | 0.4 | 5 | 1.8 |
| ወንድ | | 0.5 | 0.9 | 4.9 | 2.7 |
| ድምር | | 0.9 | 0.5 | 5.2 | 2.1 |

ሴት ወንድ ድምር


# የ2009 ዓ.ም. የክልሎች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




| | ትግራይ | አፋር | አማራ | ኦሮሚያ | ኢትዮ-ሶማሌ | ደቡብ | ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬዳዋ | አገር አቀፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 71.4 | 18.3 | 50.3 | 41.3 | 17.3 | 58.8 | 61.2 | 114.8 | 57.9 | 107.7 | 55.4 | 48.9 |
| ሴት | 76.1 | 12.9 | 56.4 | 33.6 | 11.4 | 47.8 | 46.4 | 96.0 | 51.4 | 122.9 | 47.3 | 45.2 |
| ድምር | 73.7 | 15.9 | 53.3 | 37.5 | 14.7 | 53.4 | 53.9 | 105.9 | 54.7 | 115.6 | 51.3 | 47.1 |

# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን

## በ2009 ዓ.ም. ከ1ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪዎችን ብዛት የሚያሳይ




# የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት





# ከአለም አገሮች በጣም ዝቅተኛ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሣትፎ፣

ማንበብ፣ መፃፍና ማስላት የሚችሉ ጎልማሶች የተሣትፎ መጠናችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር




# ዋና ዋና ችግሮች

- ፕሮግራሙን ለመምራት በየደረጃው የተቋቋሙት የቦርድና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አለመግባት፤
- መርሀግብሩን ለትምህርቱ ሴክተር ብቻ መተው ፣
- ተገቢው አደረጃጀት የሌለው መሆኑ፣
- ሥልጠናው ከጐልማሳው ሕይወት ማለትም ግብርና፣ ጤና፣ የሕይወት ክህሎት፣ ወዘተ. ጋር የተቆራኘ አለመሆን፣
- ማንበብና መጻፍ ላይ ማተኮር፣
- ተአማኒና ወቅታዊ መረጃ አለመኖር፣
- ለፕሮግራሙ ግብአቶች (አመቻአእና ባለሙያዎች) አለመሟላት ወዘተ፣

# ብቃትና ጥራት


# እጅግ አሳሳቢ የሆነ ብክነት የሚታይበት የትምህርት ውስጣዊ ብቃት

የመጀመሪያ ደረጃ የማጠናቀቂያ ምጣኔአችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር




# በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን ያላሳካ የተማሪዎች የመማር ውጤት


## የ4ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /50% እና በላይ ውጤት ያመጡ/



## የ8ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /50% እና በላይ ውጤት ያመጡ/



## የ10ኛ ና የ12ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /ከ 50% በላይ ውጤት ያመጡ/



# ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ምላሽ የማይሰጥና መስተካከል ያለበት ሥርዓተ-ትምህርት


- ተግባር ላይ ከማተኮር ይልቅ በንድፈ-ሃሳብ ላይ የታጨቀ መሆኑና ለፈተና የማዘጋጀት መርህ የሚከተል መሆኑ፣
- በሁሉም እርከን ያለው ሥርዓተ-ትምህርት አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን መሠረት ያላደረገ፣
- በየጊዜው እየተፈተሸ የማይከለስ፤
- የአገር በቀል የዳበረ የእውቀት ክምችትን በአግባቡ ያካተተ  ተለማጭ ሥርአተ ትምህርት አለማዘጋጀት፣
- ስለቴክኖሎጂና ስለሥራ ፈጠራ በቂ ትውውቅ፣ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው አለመደረጉ፣
- ለብዝሃነት የሰጠው ቦታ እጅግ አናሳ መሆን፣

## የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ያልቻለ የመምህራን ምልመላና ዝግጅት

- ከ2006 እስከ 2009 በተካሄዱ የሙያ ፍቃድም ምዘናዎች ምዘናውን ከወሰዱት ውስጥ፤
  - 140,435 የመጀመሪያ እና
  - 24,063 ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውስጥ


  **የመቁረጫ ነጥቡን በማሟላት ያለፉት 22% መምህራን ብቻ ናቸው፡፡**
- በ222 የገጠር፣ በ125 የከተማ በድምሩ በ347 ናሙና ት/ቤቶች በተደረገው ጥናት፤
  - ወደ **12% ያህሉ** የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ያለምንም በቂ ምክንያት **ከት/ቤት ይቀራሉ**፤
  - **28% ያህሉ በት/ቤት ውስጥ እያሉ ክፍል ውስጥ አይገቡም፤**
  - **7% ያህሉ** ከዚህ በከፋ ሁኔታ **በክፍል ውስጥ ያሉ ግን የማያስተምሩ** ናቸው።
  - በአጠቃላይ ሲታይ በክፍል ተገኝተው በአግባቡ የሚያስተምሩት 51% ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡

# በ2009 ዓ.ም. ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመከታተል ፈተና የወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውጤት




# እጅግ አሳሳቢ የሆነ የትምህርት ቤቶች ሁኔታ

## ከ2006-2008 የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ደረጃ



# ከ2006-2008 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ደረጃ



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን





# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን





# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን



# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና









# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ችግሮችና ተግዳሮቶች

- የተደራሽነት ችግር ያለበት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ
- ከኢንዱስትሪው ፍላጐት ጋር ያልተሳሰረ የሙያ ደረጃ ምደባ
- ኢንዱስትሪው በእምነት ያልተቀበው የትብብር ስልጠና እና ባለቤት ያልሆነበት የብቃት ምዘና
- የሥልጠና ጥራትን ማረጋገጥ ያልቻለ የአሠልጣኝ ምልመላና ዝግጅት
- በበቂ እውቀት ላይ ያልተመሠረተ የቴክኖሎጂ ሽግግር
- ቅንጅት የጐደለው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት
- በተለያዩ ችግሮች የተወሳሰበ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አደረጃጀትና አመራር
- በቂ ትኩረት ያልተሰጠው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ስርዓት

# ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ያላረጋገጠ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና




# የ2009 ዓ.ም. በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብዛት




| | ትግራይ | አፋር | አማራ | ኦሮሚያ | ኢትዮ-ሶማሌ | ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | ደቡብ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬዳዋ | አገር አቀፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የወረዳ ብዛት | 52 | 35 | 182 | 333 | 83 | 21 | 168 | 14 | 9 | 117 | 13 | 1027 |
| የተቋም ብዛት | 25 | 5 | 89 | 147 | 10 | 5 | 50 | 2 | 6 | 26 | 2 | 367 |

# በ2009 ዓ.ም. ከመደበኛ ሥልጠና ውጪ በየሥልጠና ዘርፎቹ ለመመዘን ፍቃደኛ የሆኑና የተመዘኑ እንዲሁም ብቁ የሆኑ በ%



# የከፍተኛ ትምህርት





# የከፍተኛ ትምህርት ችግሮችና ተግዳሮቶች


- ከፍትሐዊነት አንፃር ሴቶች፣ አካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች፣ የአርብቶ አደርና የታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች ተሣትፎ ዝቅተኛ መሆኑ::
- ከዩኒቨርስቲዎች መስፋፋት ጐን ለጐን የመምህራን ምልመላ፣ ጥራትና የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ብዙ ችግሮች አሉበት፡፡
- ብቁ ምሩቃን ማፍራት የተሳነው የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት
- የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ዋናው ችግር ከሕይወት ክህሎት ጋር ያልተዛመደና ለሥራ የሚያዘጋጅ አይደለም፡፡
- የዩንቨርሲቲዎች ስራ አመራር ቦርድ ተገቢ ድርሻውን አለመወጣት፡፡

የቀጠለ...


- ጥናትና ምርምርን በተመለከተ መንግሥት ለጥናትና ምርምር የሚመድበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም በተግባር የሚታየው የጥናትና ምርምር ሥራ ግን በጣም ውስን ነው፡፡
- የሚጠኑ ጥናቶችም፤
  - ከሕብረተሰቡ ችግር ጋር አለመተሳሰር፣
  - ከመማር ማስተማሩ ጋር አለመዛመድ፣
  - አዳዲስ መምህራን የጥናትና ምርምር ክህሎት አለመኖር፣ የጥናትና ምርምር ግብአቶች አለመኖር፣ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡
- መንግሥት ለዩኒቨርስቲዎች ከፍተኛ በጀት እየመደበ ያለ ሲሆን ትግበራው ላይ ከፍተኛ ብክነት የሚታይበት ነው፡፡
- የሚመደበው በጀትም በአብዛኛው ለአስተዳደር እንጂ በዋናው ተልእኮ ለሆኑት የመማር ማስተማር፣ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት አይደለም፡፡

# ለሴቶችና ልዩ ፍላጐት ላላቸው ወገኖች ትኩረት ያልሰጠ የከፍተኛ ትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት


## ከ2005 እስከ 2009 ዓ.ም. የቅድመ ምረቃ ተሣታፊዎች በአሃዝ



## የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎአችን ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር በ%




# የ2009 ዓ.ም. የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ጾታ ምጥጥን



# ጥራትና አግባብነት ያላረጋገጠ የመምህራን ብቃት

## በ2009 ዓ.ም. ለዩኒቨርስቲ መምህርነት ተፈትነው 50% እና በላይ ውጤት ያመጡ የዩኒቨርስቲ የቅድመ ምረቃ ምሩቃን

50% እና በላይ ውጤት ያመጡ



| | እንግሊዝኛ | ሒሳብ | ፊዚክስ | ኬሚስትሪ | ባዮሎጂ | ኢኮኖሚክስ | ጂኦግራፊ | ታሪክ | ማኔጅመንት | አካውንቲግ | የተፈ.ሀብት አስ./NRM/ | የግብርና ኢኮኖሚክስ | እጽዋት ሳይንስ | የእንስሳት ሳይንስ | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድምር | 3.48 | 1.30 | 4.61 | 9.20 | 64.68 | 2.65 | 20.78 | 3.77 | 56.98 | 8.37 | 63.98 | 59.85 | 45.66 | 26.58 | 27.79 |
| ሴት | 2.86 | 0.00 | 1.45 | 2.64 | 45.19 | 0.99 | 9.74 | 1.06 | 35.94 | 1.66 | 36.50 | 40.00 | 21.29 | 11.70 | 17.67 |
| ወንድ | 3.90 | 2.17 | 6.49 | 13.45 | 80.39 | 2.84 | 25.90 | 5.26 | 62.68 | 9.53 | 74.12 | 65.42 | 55.44 | 30.41 | 31.54 |

ድምር ሴት ወንድ

# የትምህርት አመራርና አደረጃጀት

- ከወቅቱ ጋር ያልተሳሰረ የትምህርት ፍልስፍና/ዓላማ
- የሕጻናትን እድገት ከሥራ አላም ጋር ያላገናዘበ የትምህርት መዋቅር
- በቀጣይነት ራሱን እያበቃ የማይሄድና ለሌሎች አቅም መሆን ያልቻለ የትምህርት አመራርና አስተዳደር
- በችግር የተወሳሰበ የሀብት አቅርቦትና አጠቃቀም
- ወቅታዊና ተአማኒነት የጐደለው የትምህርት መረጃ ሥርአት
- ከፖሊሲው ያፈነገጠ አተገባበር

# የትምህርት እርከን

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | እስከ ጣሊያን ወረራ | የተለያየ ነበር | |
| 2 | 1928 - 1933 | 1 – 4ኛ | አንድ እርከን |
| 3 | 1934 - 1942 | 1 – 6ኛ | አንድ እርከን |
| 4 | 1943 – 1956 | 1 – 8ኛ<br>9 –12ኛ | ሁለት እርከን<br>(8 ፡ 4) |
| 5 | 1957 – 1984 | 1 – 6ኛ<br>7 – 8ኛ<br>9 – 12ኛ | ሶስት እርከን<br>(6 ፡ 2 ፡ 4) |

# የትምህርት ቋንቋ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ከጣሊያን ወረራ በፊት-------- | ፈረንሳይኛ እና ሌሎችም |
| 2 | በጣሊያን ወረራ ወቅት-------- | ጣልያንኛ |
| 3 | ከጣሊያን ወረራ እስከ 1956- | እንግሊዝኛ ( አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት) |
| 4 | 1965 – 1984------------- | ከ1 – 6 አማርኛ<br>ከ7ኛ በላይ እንግሊዝኛ ( ፈረንሳይኛ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት) |
| 5 | ከ 1984 በኋላ ------------- | አማርኛና እንግሊዝኛ<br>50 የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች |

# የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የትምህርት ደረጃ በንጉሱ ዘመን

| ዓ.ም. | የትምህርት ማስረጃ | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|
| 1944 – 1954 | ሰርቲፊኬት | 6+1 |
| 1955– 1965 | ሰርቲፊኬት | 6+1<br>7+1<br>8+1 |
| | ዲፕሎማ | 8+4<br>9+3 |

# የመምህራን ትምህርት ፕሮግራም በደርግ ዘመን

| ክፍል | የትምህርት ማስረጃ | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|
| ከ 1 -6ኛ | ሰርትፊኬት (100%) | 12+1 |
| ከ7 – 8ኛ | ሰርትፊኬት (70%) | 12+1 |
| | ዲፕሎማ (30%) | 12+2 |
| ከ 9 -10ኛ | ዲፕሎማ (35%) | 12+2 |
| | ድግሪ (65%) | 12+4 |
| ከ 11-12ኛ | ድግሪ (100%) | 12+4 |

# Technical and political factors divert Schools, Teachers, and Families from a focus on Learning




Source: WDR 2018 team.

# Coherence and Alignment toward Learning



# ማጠቃለያ

- የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በበርካታ ችግሮችና ተግዳሮቶች የተሞላ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

- የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በንድፈ-ሃሳብ ላይ እንጂ ተግባር፣ ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም፤ የምዘና ሥርአታችንም እውቀትን ብቻ የሚመዝን ነው፡፡ ዜጐችንም በ16 አመታቸው የሁለተኛ ደረጃ እንዲያጠናቅቁ በማድረግ ከትምህርትና ሥልጠና ሥርአቱ ውጪ እያደረግናቸው ነው፡፡

- እስካሁን እየተገበርን ያለው የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሥራ ፈላጊ እንጂ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ እየፈጠረልን አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያትም ሕብረተሰቡ በትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን የጥራትና የተገቢነት ጥያቄ እያነሳ ይገኛል፡፡ በተለይ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ልጆች ከሥራ አፈናቅለን የተሻለና የሰለጠነ ትውልድ እንፈጥራለን ብለን ወደ ትምህርት ቤት አምጥተን ከተማሩ/ከሠለጠኑ በኋላ ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው ሥራ ሲያግዙና ሥራ ሲፈጥሩ አይታዩም፡፡

# ማጠቃለያ…

- በትምህርትና ሥልጠና የሚያልፈው ትውልድ ከትምህርትና ሥልጠናው እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ የምስክር ወረቀቱን/ዲፕሎማውን ይዞ መገኘትና ዲፕሎማ አምላኪ ሆኗል፤ በሂደቱም የኩረጃና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ጐልቶ ይታያል፡፡
- በትምህርትና ሥልጠና ያሉት ሁሉም ዘርፎችና ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶና ተናበ አይሰሩም፡፡
- የምርምርና የቴክኖሎጂ ሥራችንም ጐልብቶ ኢኮኖሚው በሚፈለገው መጠን እያገዘ አይደለም፡፡
- ከሌሎች አገራት ጋር ሲነፃፀር የትምህርትና ሥልጠና ጥራታችን በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ራሳችንን የምናይበት ሥርአት አልዘረጋንም፡፡

# ማጠቃለያ...




**ስለዚህ የፍኖተ ካርታውን ግኝቶች ይዘን ከ2011 ጀምሮ ወደ ስር ነቀል ለውጥ መግባት አገራችን ከኛ የምትጠብቀው ስትራቴጂና ወቅታዊ ጉዳይ ነው፡፡**


አመሰግናለሁ።